16-08-2011

# <u>የሁለቱም አክራሪ መስመሮች ይጎዱናል</u> !!!

ከብስራት ኢብሳ (ሆላንድ)

ሰሞኑን የግንቦት ሰባትን እና የኦነግ-ኦብነግን ንግግር አስመልክቶ በዲያስፖራው ይህን በሚቃወሙና በሚደግፉት መሃል ሞቅ ያለ የተፋፋመ ትግል እየተካሄደ ነው፡፡ ሁለቱም ክፍሎች ዝም ያለው ብዙሃንን(silent majority) ከጎናቸው ለማሰለፍ የሚቻላቸውን ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ መሃል ለይ ያለውም እንደተለመደው ንፋሱ ወደሚያደላው እያመዘኑ ዥዋዥዌውን መጫወት ቀጥሎዋል፡፡ ሁለቱም ክፍል ብእራቸው እስከሚነጥፍ መጻፋቸውንና ለመጨርሻው ፍልሚያ ''ለክፉ ቀን'' የስቀመጧቸውን ጠንካራ ደጋፊዎቻቸውንና ሃዋሪያቶቻቸውን በየመድረኩና በየሚዲያው ያሰማሩበት ወቅትላይ ነን፡፡

የአገዛዙ ወኪሎችም ሆኑ በዚህ ልዩነት እናተርፋለን ብለው የራሳቸውን የቤት ስራ በትጋት የሚሰሩትም ታታሪዎች ሁኔታውን ሳይጠቀሙበት እንዳያመልጣቸው ፣ በጥንቃቄ እሳቱ ቀዝቀዝ የሚልበትን ስፍራ እያዩ ቤንዚኑን ጠብ እያደረጉ ፣ ማቀጣጠሉን ተያይዘውታል፡፡ ሁለቱም ወገኖች ይህንን የውቁታል ፣ ''የዛሬን ያውጣን እንጂ'' እንኩዋን ወያኔ ሰይጣንም ይሁን፣ የሚደግፈን ፣ ሰፈራችንን እስካሞቀና ሚዛን እስከደፋን ብለው የወሰኑ ይመስላሉ፡፡

የግንቦት ሰባትንና የኦነግ/ኦብነግ <u>ንግግር መጀመር</u> ከሚደግፉት ዉስጥ አንዱ ነኝ፡፡ የመጀመርያው የምደግፍበት ምክንያት፣ ለረጅም ጊዜ የበጋ እንቅልፍ ላይ የነበሩ የተቃዋሚ ድርጅቶችን ከእንቅልፋቸው አንቅቶ እያራወጣቸው ነው፡፡

ይህንን ንግግር መጀመር የምደግፈው፣ ለብዙ ጊዜ ተለያይተው ይሻኮቱ የነበሩ ድርጅቶችን አብሮ አቁሞዋል፡፡ አይንህ ላፈር ተባብለው በጎሪጥ ይተያዩ የነበሩትን አቀራርቧል፡፡ ተኮራርፈው የነበሩ ግለሰቦችን አስታርቁዋል ፡፡ ሁለት ሦስት ቦታ ተከፋፍለው ይደባደቡ የነበሩትን ሰላሙን አስፍኖዋል ፡፡ ለዓመታት እባካችሁ ተባበሩ፤ ግንባር ፍጠሩ፤ አብራችሁ ቁሙ ፣ ተቻቻሉ ፣ ተብሎ ያ ሁሉ ልመና ፣ ያ ሁሉ ግፊት ሲደረግ ጆሮ ዳባ ያሉት ፣ ዛሬ በዚህ ስብሰባ መጀመር ምክንያት ፣ ሽማግሌ ሳይላከባቸው አስታራቂ ሳያስፈልጋቸው ፣ ቀጠሮ ሳይዙ ፣ አጀንዳ ላይ ሳያሰፍሩ ፣ ስንቄን ማቄን ሳይሉ ቆፍጠን ብለው እጅጌያቸውን ሰብስበው ተነስተዋል ፣ ከዛ ሁሉ ልፋት ቦሃላ እንድዚህ ባጭር ጊዜ ዉስጥ ሊያፋቅርና፣ ከእንቅልፋቸው እንዲነቁ ለረዱን ድጋፍ ካልሰጠን ለማን ልንሰጥ ነው? ብዬ አሰብኩና አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ መተከዝ ጀመርኩኝ ፡፡
ይሄ አንድነት ካሁን ቀደም በተደጋጋሚ ያየነው አይነት እንዳልሆነ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ በተለያየ ያለፈው ታሪካችን የውስጥ ግጭቶች ሲካሄዱ ቆይቶ ፤ የውጭ ጠላት ፣ወራሪ

የመጣ በመሰለን ወቅት ልዩነትን ለጊዜው አስወግደው ፣ በጋራ ጠላትን ካባረሩ ቦሃላ እንደገና ፍልሚያው ከቆመበት ይቀጥላል፡፡

ይህ ተመሳሳይ ሁኔታ ቅርጹን ይዞ ባህርዩን ለውጦ የእኔ ትውልድ አዲስ ስም ውጥቶለት ``የጠላቴ ጠላት ወዳጄ`` ፖለቲካ ሆኖ ይሄው ለእርስ በእርስ ለመጎዳዳት በሁሉም ስፍራ አላግባብ እየተጠቀምንበት ባላንበት ሲያስረግጠን ዓመታት እያስቆጠረ ነው ፡፡
ዛሬ በግልጽ እንደምናየው ፣ መሰረታዊ ልዩነት እንኳን ሳይኖረን ፣ ግባችንና ዓላማችን አንድ ሆኖ ፣ ባካሄድ ፣ በዘዴ አመራረጥ ፣ በመሪዎች ሽኩቻ ምክንያት ካላበቂ ምክንያት እርስ በርስ እንደ ጠላት መተያየት ቀጥለናል፡፡ ለመገንባት ከመሰባሰብ ይልቅ የማንፈልገውን ነገር ለማፍረስ ባስቸኳይ ለመሰባሰብ ሰብሳቢ ወይም ጋባዥ አያስፈልገንም፡፡ የምንቃወመውን ተባብረን ካፈረስን ቦሃላ ፣ ወዲያው ለስላሳው ሽኩቻ ከክረምት/በጋ እንቅልፍ ጋር መቆዘሙ ይጀመራል ፣ ሌላ ዙር የሚያነቃን እስከሚመጣ ፡፡ መኖራችንን የምናስመሰክረው ሌላ የሚሞክር፣ የሚሰራ ብቅ ሲል ብቻ ይመስላል ፡፡

በኢትዮ-ሚድያ ድህረ ገጽ ፣ ``በክፍፍሉ መሃል እነሆ አዲስ መፍትሄ``በሚል ዘገባ ፣ ኤሎን እንደጠቆሙት ፣ በዚህ ግርግር አገዛዙ እንደተረሳና በዚህም ክፍፍል እንደተጠቀመ ግልጽ ነው፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በአምስተርዳም ከተማ የእሳት ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ በጠራው ስብሰባ ላይ የኦነግ ተወካይ ባይኖሩም ፣ ከተሰብሳቢዎቹ እራሳቸውን በኦነግ ደጋፊነት እራሳቸውን ያስተዋወቁ አስያየት አዳምጫለሁኝ፡፡ ከዚያም በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌና በሙቶ አለቃ አያል ሰው መሃል የተካሄዱትን ውይይቶች በኢንተርኔት ተከታትዬ ፣ ኦገስት 13 እና 14 ቅዳሜና እሁድ የሙቶ አለቃ አያል ሰው ሁለት ፓልቶክ ክፍል ተጋብዘው የተወያዩትን ተከታትያለሁኝ ፡፡ ባጠቃላይ ላለፉት ወራት በዚህ ጉዳይ ጀርዩ እስከሚደነቁር የተለያዩ ውይይይቶችን ተከታትዬ ብዙ ትምህርት አግኝቼበታለሁኝ ፣ብዙ ትዝብትም ታዝቤያለሁኝ  የራሴ የደረስኩበትን መደምደሚያ ለወገኖቼ አካፍዬ ፣ የበኩሌን ትንሽ አስተዋጽኦ ለማድረግ ፣ ወይንም ተሳስቼም ከሆነ ለመማር በግልጽ ሃሳቤን ለማስቀመጥ እሞክራለሁኝ፡፡

ከሁሉ ነገር በፊት በግሌ ያለኝ አቋም ፣ ችግርን ተቀራርቦ መነጋገር መጀመር መደገፍ ብቻ ሳይሆን መበረታታት ያለበት ጉዳይ ነው ፡፡ ማንኛውም ድርጅት በሚመቸው መንገድ የመደራጀትም ሆነ ከሚፈልገው ጋር የመነጋገር ፣ የመሰብሰብ መብት አለው ፡፡ ይህንን መብት ማንም ሊሰጥና ሊነሳ አይችልም ብዬ አምናለሁኝ፡፡
ይህ ተቀራርቦ አለመወያየት ጎጂ ልማድ ለረጅም ዓመታት ስር ሰዶ ፣ በድርጅት ውስጥ ሊፈጠር በሚችል ጤናማ የመስመር ልዩነትም ሆነ ፣ በድርጅቶች መሃከል በሚፈጠሩ ፣ ልዩነቶች ዙርያ በሰከነ መንፈስ ተወያይተው መነጋገር ሲገባ ፣ አሁን ባላንበት ደረጃ ፣ ከኩርፍያም ሆነ ከሽኩቻ አልፈው ፣ ከመሰዳደብ ከፍ ብለው፣ ከመካሰስ ተሸጋግረው ፣ የቀራቸው መደባደብ ብቻ ነው፡፡ አብዛኞቹ የተቃዋሚ ድርጅቶች ከባህር ማዶ መሆናቸው

እንጂ ፣ ሃገር ውስጥ በደጋፊዎቻቸው መሃል ቢሆኑ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ማሰቡ እራሱ ይዘገንናል፡፡

ሆኖም ይህንን ደካማ ጎኖቻችንን በመጠቀም አክራሪዎች ፣ ወያኔን ጨምሮ ፣ የራሳቸውን እቅድ በስራ ላይ ለማዋል ፣ እኛኑ መስለው ተባ ድነውም ሆነ ብቻቸውን ተደራጅተው፣ በመሃከላችን ያለውን ልዩነት እየተጠቀሙ ፣ ይበልጥ ልዩነቱ እንዲሰፋና ፣ ትግሉ አቅጣጫውን እንዲለውጥ እየተደረገ ነው፡፡ አሁን በደረስንበት ደረጃ እንዴት በጋራ ወያኔን አስወግደን ፣ የህግ የባላይነት ያለበት ፣ የሁላችንም መብት እኩል የሚከበርበት ስርዓት በጋራ ለማምጣት ከመታገል ይልቅ ፣ ያለው መለስተኛ ልዩነት ይበልጥ እየከረረና ችግሩ ወደ ቡድንና ሕዝብ፣ በሁለት ጽንፈኛ መስመሮች እየተገፉ ነው፡፡

ሁለቱም አክራሪ መስመር ይጎዳናል ብዩ ስጀምር ፣ በሁለቱ ፅንፈኛ አመለካከት መሃል ፣ አብዛኛው ሕዝባችን የያዘው ብዬ የማምንበት ሌላ ትክክለኛ ሕዝብዝዊ መስመር እንዳለ እንደተጠበቀ ሆኖ ነው፡፡

በመጀመሪያ ፤ የኢትዮጵያ አንድነት፣ ወይም ፣ አንድ ኢትዮጵያ ፣ ብለን የምናምን ሃገራችን ኢትዮጵያ ስንል ፣ ባጭሩ ዘርና ፣ ሃይማኖት፣ ሳይለይ በረጅም ዘመን በበጎም ይሁን በከፉ ፣ በችግርም ይሁን በድሎት ፣ አኩሪም ሆነ ፣ ያልሆነ፣ አብረን የገነባነው በጋራ የሚያስተሳስረን ታሪክ አለን ብለን ስለምናምንና ፣ለዚህም መሰረቱ፣ መሬትና የሕዝብ ትስስር ነው ፡፡

የቋንቋችን ፣ የባህላችንና ፣ የሃይማኖት እምነታችን መብዛት ፣ ጌጣችን ሃብታችን ልዩ የሚያደርገን እውነታ (ክስተት) ስለሆነ ልንኮራበት እንጂ ልናፍርበት አይገባም፡፡ እንደማንኛውም ሃገር ታሪክ ፣ በእኛም ሃገር፤ የሃገር ግንባታ ሲካሄድ ሊደርሱ የሚችሉ ችግሮች ፣ በደሎች ደርሰዋል ፡፡ ታሪክን ለፖለቲካ ጥቅም ለማዋል ካልፈለግን በስተቀር ፣ አልፎ አልፎ እንደምንሰማው ፣ ድሮ በዛን ወቅት የሰው ልጆች የእውቀትና ፣ የስልጣኔ ደረጃው ባልዳበረበት ዘመን ለተሰሩት ስህተቶች ፣ አሁን በሃያ አንደንኛው ክፍለ ዘመን በደረስንበትን የእድገትና የአስተሳሰብ ደርጃ ጋር እየመዘንን ሚዛኑን ያልጠበቀ ፍርድ ለመስጠት መሞከር ቅንነት ይጎድለዋል ብዩ አምናለሁኝ፡፡

ይህ ማለት ግን ያለፈውን ስህተት አርመን ፣ ቂም በቀልን አስወግደን፣ የነበሩትን ችግሮች በጋራ መግባባት ላይ ደርሰን ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የጋራ ሃገራችንን ወደ መገንባቱ ማተኮር የለብንም ማለት አይደለም ፡፡ ባለፈው ላይ ማን ምን አደረገ በሚለው ላይ ቢያንስ ከሁሉም ወገን ፣ እውነትም ይሁን ሃሰት ፣ ተጋኖም ይሁን ተቆራርጦ በበቂ ፣ ተጽፎዋል፤ ውይይቶች ፣ ክርክሮች ተካሂደዋል፣ ብሶቶች ተሰምተዋል ፡፡ ይሄ ሁሉ ሆኖ ምንም የቋጨነው ፣ ተስማምተን የደረስንበት ስለሌለ ፣ ችግሩ ሁሌ እያመረቀዘ በመሃከላችን ያሉት አክራሪዎች በዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ወደ ``ዘመናዊ የመሳፍንት ዘመን `` እየገፉን ነው፡፡

በተጨማሪም በተለያዩ ምክንያቶች ለሃገራችን ቀና አመለካከት ከሌላቸው ባእዳን መንግስታትና ፣ ሕዝብን በመከፋፈል ስልጣን ላይ ለመቆየት ከሚሻው አገዛዙን ጨምሮ ፣ ያሳለፍናቸውንና ያሉንን ልዩነቶች በአሉታዊ ጎኑ ብቻ ከሚገባው በላይ ያለፈውን ቁስል በመነካካት ፣ አንድነታችንን ሲከፋፍሉና ኖረዋል፣ አሁንም እያካሄዱ ነው፡፡

ትንሽ የደረስንበት በጎ ነገር ቢኖር ፣ የኔ ትውልድ ፣ ከትግል ልምድ እጥረት ከውጭ ያገኘነውን እውቀት ከሃገራችን እውነታ ጋር ሳናመዛዝን ከሌላ ሃገር ልምድ የወሰድናቸውም የነበሩ የተሰሩ ስህተቶች በብዙዎች ዘንድ በውይይትና ፣ የአቅዋም መስተካከል (በመግባባት) እየተደረሰባቸው የብዙዎች አስተሳሰብ ከዛሬ ሰላሳና አርባ አመታት በፊት ከነበረው በመጠኑ እየተቀየረ ነው ፡፡

ባጭሩ ትላንት በኔ ትውልድም ሆነ "በነጻ አውጪዎች" አካባቢ ይገፋ የነበረው የኮሎኒና የብሄር ጥያቄ እስከመገንጠልና ፣ ለጭቆናው ተጠያቂው አንድ ብሄር ብቻ እንደነበር.... ተወስዶ የነበረው አቅዋም ፣ ዛሬ ከብዙ ክርክሮችና ውይይቶች ቦሃላ ፣ አክራሪዎቹን ትተን፣ በአብዛኛው በነበረው የስርዓት እና የመደብ ልዩነት፣የነበረውን የመሬት ይዞታን ጨምሮ በሁሉም ብሄር ዉስጥ ጨቋኝና ተጨቋኝ እንደነበሩና ፣ ብዙ ብሔሮችም በራሳቸውም ብሄር ጭምር ይጨቆኑ እንደነበር ፤ ለዚህም አንድ ብሄር ብቻውን ተጠያቂ ሊሆን እንደማይችል በከፊል ተቀባይነት ማግኘቱን ስናዳምጥ ፣ ቢያንስ በጽንሰ-ሃሳብ ደረጃ በዚህ አስቸጋሪ ጥያቄ አካባቢ አንዱ ምዕራፍ ላይ ወደ የጋራ መግባባት እየተቃረብን ነን ማለት ይቻላል ፡፡

ይህንን ብዙዎች የሚጋሩትን እውነታ፣ ወይም የጋራ አቅዋም ፣ በሁለት ረድፍ የተሰለፉ ፣ አክራሪ አመለካከት ያላቸው ምሁሮቻችንና ፣ (አገዛዙን ጨምሮ) ይህ ከላይ የተገለጸውን ጽንሰ ሃሳብ ፣ ፅንፈኛ አቅዋማቸውን ስለሚያበላሽባቸው አይቀበሉትም፡፡ እነዚህ በሁለት የተከፈሉት፣ የዓላማና ግብ ልዩነትና ፣ የባህርይ አንድነት ያላቸው፥ ሁለቱም እኩል ለአንድነታችን አደገኛ ስለሆኑ አካሄዳቸውንና በጥንቃቄ መመርመር አለብን፡፡

ወደድንም ጠላንም በህብረተሰባችን ዉስጥ ፣ ቀዳሚ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ሚና የሚጫወተው ምሁሩ ነው፡፡ የምሁሩ ጤናማ ራእይ በወደፊቱ የሃገራችን ሁኔታ ላይ ከፍተኛ አወንታዊ ተጽእኖ አለው፡፡ እነዚህም ውድ ሃገር በቀል ምሁራኖቻችን ለውድ ሃገራችን፣ ቀን ከለሊት ያለ እርፍት ሲለፉ ሲደክሙ ስናይ አድናቆታችን ከፍ ያለ ነው ፡፡ በሃገራችንም አሁን በምናየው ተጨባጭ ሁኔታ የሃገራችን ምሁሮች ትግሉን በማቀነባበርና በማደራጀት የሚጠበቅባቸውን እየሞከሩ እንዳሉ ሁሉ፣ በአንጻሩም በአሉታዊ ጎኑ ለሕዝባችን ሳይሆን ለራሳቸው ማን አህሎኝነት (ego) ፣ በምክንያት ሳይሆን በስሜት፤ ለሃገር ሳይሆን ለጉጥ፤ ለታሪክ ሳይሆን ለዝና ፣ ለሃገር የጋራ ጥቅም ሳይሆን ለቡድንና ለግል ስልጣን ቅድሚያ በመስጠት በሁለት ተጻራሪ መስመር የቆሙ ጥቂት አክራሪ ምሁሮች ምክንያት ፣ ያሉት ልዩነቶች እየተናፈሱ እንዲካረሩና ፣ በሕዝባችን መሃል ይበልጥ

ጥርጣሬና ጥላቻ እንዲባባስና ፣ ትግሉም አቅጣጫውን እንዲስት እየገፉት ነው ፡፡ ለሕዝባችን ጥያቄ መልስ ከመስጠት ይልቅ ፣ በጣም ኋላቀር በሆነ ፣ የመሬት የይገባኛል ነትርክ ዉስጥ አስገብተውን ሁለት ጎራ ለይተን እንድንጨቃጨቅ እየገፉን ነው፡፡ ከሕዝባችን ጎን የቆማችሁ መሁራንና ፣ ታጋዮች በዚህ እሰጥ አገባ ፣ የመሬት የይገባኛል ጥያቄ ዉስጥ ሳትጠለፉ እስካሁን ያልተመለሰውን የሕዝባችንን ጥያቄ በጋራ ሆናችሁ እኛንም አስተባብራችሁ ለመመለስ አብረን እንታገል፡፡

የአብዛኛው የሰርቶ አደሩ ሕዝባችን መሰረታዊ ችግር ፣ አገዛዙ ከሚያደርስበት በደል በተደራቢ፣ የኑሮ ውድነት ፣ ግብር ፣ የማዳበርያ እዳ፣ የዝናብ መጥፋት ፣ ድርቅ ፣ እረሃብ፣ በሽታ ፣ ....ወዘተ እንጂ ፣ ጸሃፊው እንዳሉት የመቶ ዓመት ታሪክ እያነሳ ጉልበቱን የሚያጠፋበት ፣ ፍላጎቱም ፣አቅሙም ፣ ጊዜውም የለውም፡፡ እነዚህ በአሉታዊ(negative) ሚና የሚጫወቱ ፣ የታሪካችንን በጎ ጎን ሳይሆን ፣ የደረቀውን ጠባሳ እየፈቀፈቁ በሕዝባችን መሃከል ቂምና ቁርሾ እንዲስፋፋ ሌት ከቀን የሚለፉ በሁለት ተጻራሪ ረድፍ የተሰለፉ ጥቂት፣ ግን ጫሂ(noisy) አክራሪ ምሁራን ናቸው፡፡

የመጀመርያዎቹ ፣ ኢትዮጵያ በምትባል ኢምፓየር ኮሎኒ ሆነን ስለተገዛን ከመገንጠል ዉጪ ሌላ ምንም መፍትሄ ሊኖር አይችልም ብለው ደምድመው፤መገንጠልን ብቻ እንደ የመጨረሻ ዓላማና መፍትሄ አድርገው የቆሙና፡፡ በተካሄደው የሃገር ግንባታ ተፈጽሟል ብለው የሚያቀርቡት አሉታዊ ገጽታውን ብቻ ነው፡፡

ሁለተኞዎቹ፣ በኢትዮጵያ አንድነት ሽፋን ውስጥ ቀፎ ሰርተው ተመሳስለው፣ በተግባር ግን የአንድ ጎጥ ወይም ቡድን ጥቅም ብቻ የሚገፉና፣ ጠቅላላ ሕዝባችንን በእኩልነት ማየት ችግር ያለባቸውን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ክፍሎች በግልባጩ የሚነግሩን አወንታዊ ገጽታ ብቻ እንደነበር ነው፡፡

በነዚህ ሁለት ጎራ በተሰለፉ አሳሳች ምሁራን ቅስቀሳ ተሳስተው ፣ ውድ ሃገራቸውን የካዱ ፣ ታሪክን በመጥፎ ጎኑ ብቻ እንዲያዩ የተወናበዱ፣ በዘር ፣ በጎሳ እንዲያስቡ የተቃኙ ባጠቃላይ በሕዝባችን መሃል ጥላቻ በመንዛት አብሮ በሰላም እንዳይኖር ችግር እየፈጠሩ የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም ፡፡

ሁለቱም የራሳቸውን ግልጽም ይሁን የተደበቀ ጠባብ ዘረኛና፣ ቡድናዊ ዓላማ ለማስፋፋት ፣ አንዱ የሌላውን መኖር በጣም ይፈልገዋል ፡፡ እንደ ቫየረስ ወይም ፓራሳይት፣አንዱ ካለሌላው ህይወት የለውም፡፡ምናልባት(symbiotic relationship) ባጭሩ ባጭሩ ይገልጸው ይሆናል፡፡

ሁለቱም በራሳቸው መንገድ አንዱ ሌላውን በመኮነንና በማሳጣት፣ ለውጭያዊ ምክንያታቸው እንደ ዋቢ ለማጣቀስና ፤ የእራሳቸውን የተደበቀና ግልጽ ዓላማ ለማስፋፋትና የየግል ግባቸውን ለመድረስ እንጂ ፣ ብሔራዊ መግባባት ፤ የሕዝብ መቀራረብ ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ፣ ተፈቃቅዶ ተከባብሮ በጋራ በአንድነት ችግን

ለመፍታት ዕድሉን አይሰጡም ፡፡ አንዱ በሌላው ላይ የሚያየውን ድክመት በመጠቀም አንዱ ሌላውን አግልሎ የራሱን ዘረኛ ወይም የጠባብ ቡድን ዓላማ በሌላው ላይ ለመጫን እንጂ ሁለቱም ለአንድነታችን አደገኞች ናቸው ፡፡

በጣም የሚያስገርመውና የሚያሳዝነው፣ ሁለቱም ወገኖች አንዱ ሌላውን በዘረኝነት፣ ወይም በጠባብነት ለማሳጣት የሚያቀርቡትን ምክንያቶች በሙሉ እራሳቸው ሲጠቀሙበት፣ ወይንም በተግባር ሲያደርጉት ስህተት መሆኑ አይታወቃቸውም ፡፡

ሁለቱም `` ከእኛ `` ውጪ የሚሉትን ማግለል ብቻ ሳይሆን የመረረ ጥላቻና ንቀት አለባቸው፤ የሚቆፍሩት ታሪክ ፤ የሚያገላብጡት የታሪክ መዛግብት ፤ የሚሰበስቡት ሰነድ የሚያነቡት መጻህፍት ፣ የሚያቀርቡት ዋቢና የሚጋብዙን መረጃዎች፣ በጥንቃቄ የሚመርጡት የያዙትን ዘረኛ ዓላማ የሚያጠናክርላቸውን ብቻ ነው ፡፡

ሁለቱም ``የእኛ`` ከሚሉዋቸው ውጪ ያሉትን ወገኖቻችን ፣ ስርአቱ በሚያደርስባቸው፣ ኢ-ሰብአዊ ግፍና፣ ጭቆና ፣ ወይም ተፈጥሮ በሚያደርስባቸው አደጋ አንዱ የሌላውን በደል በራሱ ሕዝብ ላይ እንደደረሰ አድርጎ አያየውም፡፡

ሁሌ ስሌታቸው በመንደር፣ በጎሳ፣ በቡድን ስለሆነ ፣ የሌላው ወገናቸው ችግር፣ ስቃይ ረሃብ እንግልት ፣ እስር ስሜት አይሰጣቸውም ፡፡ እንዲያውም ከጥላቻቸው ብዛት ፣ ``የኛ``በማይሉት ክፍል አገዛዙ በሚያደርስባቸው በደል ፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ድጋፍ መስጠት ብቻ ሳይሆን እነሱ የሚፈልጉት ዓላማ እስከሚሳካ ያለው ስርዓት እንዲቆይ ሁሉ ግልጽና ስውር የድርጊት ትብብር ያደርጋሉ፡፡

ሁለቱም አንዱ ሌላውን በመጤነት ይከሳሉ ፣ እነዚህ አክራሪዎች ``እኛና`` ``እነሱ`` የሚለውን ቃል በመጠቀም በሕዝባችን መሃል አጥር ያቆማሉ ፣ ግንብ ይገነባሉ በሕዝባችን መሃል ያለውን ድልድይ ያፈርሳሉ ፡፡ አንዱ የሌላውን ልማድ ፣ እምነት ፣ ታሪክ የሚመለከቱት ፣ የሚያቀርቡት፣በቅናት ፣ በንቀትና በጥላቻ ነው ፡፡ የግል ችግራቸውን ወደ ሕዝብ በመግፋት በዛ ውስጥ ተደብቀው ሕዝባችንን ይለያያሉ ፣ ይከፋፍላሉ ፡፡

እነዚህ አክራሪዎች ፣ ለሌላው ባህል ፣ ለሌላው ቋንቋ ፤ ለሌው አካባቢ እድገትና ብልጽግና በጎ አመለካከት የላቸውም ፤ ከራሳቸው ውጭ ብለው ያሚያስቡትን በሙሉ በጥላቻና በጥርጣሬ ስለሚያዩ ፣ በግል ከራሳቸው መንደር አካባቢ ውጪ መሄድ አይመቻቸውም ፡፡ ማህበራዊ ግንኙነታቸው ፤ የፖለቲካ አደረጃጀታቸው ፤ ባጠቃላይ አዕምሮዋቸው የተበከለው ፣ የተቃኘው ሁለቱም የሚያስቡት፣ የሚተነፍሱት ፣ የሚያስሉት በ``የእኛ``በሚሉት ጠባብ ክፍል ስለሆነ ሁለቱም ለአንድነታችን ጸሮች ናቸው፡፡ እነዚህ በቁጥር በጣም አነስተኛ የሆኑ ቡድንም ይሁኑ ግለሰቦች ከየትኛውም አካባቢ (በትውልድ) ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ የ``እኛ`` የሚልዋቸውን ከአገዛዙ ጋር እንኳን ቢያብሩ ፣ ሁለቱም አክራሪዎች ችግር የለባቸውም፡፡

በሁለቱ መሃከል ምናልባት መሰረታዊ ልዩነት ለማየት ከሞከርን ፣

የመጀመርያው፣ የማስገነጥለውን ሕዝብ እወክላለሁኝ ብሎ ካርታውን ሰርቶ ፣ ድንበሩን ከልሎ ፣ ምክንያቱን ደርድሮ ከሌላው እገነጠላለሁኝ ይላል፡፡ ከመገንጠል በስተቀር ፣ አለ የሚሉትን ችግር ፣ ከወገኖቻቸው ጋር በመቀራረብ ፣ በመወያየት ፣ ለመፍታት ምንም አይነት ፈቃደኝነት አያሳዩም፡፡

ሁለተኛው ፣ በስም ደረጃ በኢትዮጵያ አንድነት ስም ውስጥ ተጠልለው ፣ በተግባር ግን፣ከመጡበት አካባቢ ውጭ በሃገሪቷ ውስጥ የሚኖሩትን ሁሉንም ሕዝብ በእኩልነት ማየት ይቸግራቸዋል፤ የ``እኛ``ከሚሉት ውጭ ያለውን በጥርጣሬና በጥላቻ ስለሚመለከቱ በሌሎች የሚቀርቡ ማንኛውንም ፣ የእኩልነት ፣ የሰባዊ መብት ፣ የዲሞክራሲ፣የፍትህ ጥያቄ ፣ በጸረ ኢትዮጵያዊነትና በተገንጣይነት ጎራ ይመድቡታል፡፡

የመጀመርያው ክፍል እራሱን በግልጽ ነጥሎ አስቀምጦ ፣ የሱ አይነት ተማሳሳይ የመገንጠል አቅዋም ካላቸው በጎጥ ላይ በተመሰረቱ ድርጅቶች ዙርያ ሲያጠነጥን፤ ሁለተኛው እንደሚመቸው እራሱን በጎጥ ነጥሎም ይሁን ፤ በህብረ-ሕዝብ ድርጅቶች ውስጥ የራሱ ቀፎ በመስራት ፣ እንደአስፈላጊነቱ እራሱን እያመሳሰለ ፣ ቀን የአንድነት ፣ ማታ የጎጥ፣ እንደሚያመቸው ይቀያየራል፡፡

እነዚህን ባህሪያት ከዘረዘርኩኝ ቦኋላ ፣ ላለፉት ረጅም ዓመታት ፣ በሃገራችን ውስጥ የኦሮሞ ፣ የኦጋዴን ፤ የሲዳማ ...ወዘተ ሕዝብ ነጻ አውጭ ነን ብለው እንቅስቃሴ ከጀመሩ ዓመታት አስቆጥሮዋል፡፡ ከነዚህ ዉስጥ አብዛኞቹ እየደበዘዙ ባንሰማቸውም ፣ እስካሁን ድርጅታዊ ቅርጽ ይዘው በትጥቅ ትግል እንንቀሳቀሳለን የሚሉት ፣ ኦነግና ፣ ኦብነግ ናቸው፡ ባሁኑ ሰዓት ኦነግ ቢያንስ ሁለት፣ሦስት ቦታ የተከፈለ ሲሆን ከነዚህ ዉስጥ አንደኛው የኦነግ አንጃና ኦብነግን ጨምሮ ከግንቦት7 ጋር መነጋገር ጀምሮዋል፡፡ ለውይይት ያልቀረበው ሌላው የኦነግ አንጃ ይህንን ሰላማዊ ውይይት በበጎ እንደማያየውና ለማሰናከልም እየሞከረ እንደሆነ፣ ከሚያወጣቸውና አንዳንድ ቦታ ከሚያሰራጫቸው ጽሁፎች ማየት ይቻላል ፡፡

ይህ የተጀመረው ንግግር፣ ወይም ውይይት፣ ወዴት ሊሄድ እንደሚችል ፣ በምን እንደሚቋጭ ፣ ምን ድምዳሜ ላይ ሊደርሱ እንደሚችል ፣ እንኳን እኛ ፣ ውይይቱንም የጀመሩት ገና አያውቁትም ፡፡ ባጭሩ ገና የተቦካ ሊጥ ነው ፣ ዳቦ ሆኖ ይውጣ ፣ አይውጣ ከተስፋ በስተቀር ምንም የሚታወቅ ነገር የለም፡፡

ከግንቦት7 በተደጋጋሚ እንደተነገሩን ፣ በሃገራችን መሰረታዊ ጥቅሞች ላይ ውክልና ስለሌላቸው አይደራደሩም ፡፡ የራቀውን ለማቅረብ፣ ያኮረፈውን ወደ ማእከሉ ለማምጣትና ሁሉንም ያካተተ ዘለቄታዊ ሰላም ለማስፈን መሰረቱን ለማመቻቸት ነው ብለውናል ፡፡ እንዲያውም እየተነጋገርን እንጂ ትብብር አልጀመርንም፡፡ የምንነጋግረው ለአንድነታችን ችግር የፈጠረውን እስካሁን የሚያራምዱትንም ሆነ በፕሮግራማቸው ዙርያ

አብሮ ለመታገል ችግር የፈጠሩትን አቅዋሞችም ሆነ አንቀጾች ሰበው ወይም አጥፈው ለጋራ ሃገራችን ለኢትዮጵያ አብረን ለመስራት እንድንጀምርና፤ ይህም ማለት ወደፊት ለሚፈጠረው ሰፊ መድረክ ፣ ማንንም ያገለለ እንዳይሆንና ሰፊ መሰረት እንዲኖረው...ወዘተ ሲሉ ሰሞኑን በ ኢንተርኔት ውይይቱን አዳምጫለሁኝ፡፡ ለጋራ ሃገራችን አንዱ ሌላውን ማባበልም ሆነ መለመን አስፈላጊነቱ ባላምንበትም ፣ ለሃገር ሲባል ሰላምን ለማምጣት ፣ መቀራረብን ለመፍጠር ፣ ግጭትን ለማስወገድ አንዱ ሌላውን አግባብቶ ለማሳመን ቢሞክር ሊደገፍ ሊበረታታ ይገባዋል ባይ ነኝ ፡፡

አሁን በውይይት ላይ ያለው የኦነግ አንዱ ክፍል ፣ ቢያንስ ከላይ ከተጠቀሱት አክራሪዎች እራሱን ነጥሎ ፣ አንድ እርምጃ ወደፊት ቀርበው ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወገኖቻቸው ጋር ለወደፊቱ ሰፊ መድረክ አስተዋጽኦ ለማድረግ መነጋገር ጀምረዋል ፡፡

ላለፉት ጥቂት ወራት ከኦነግ አመራር ውስጥ ጥቂት የማይባሉ ፣ አልፎ አልፎ በጎ ነገሮች በወሬ ደረጃም ቢሆን እየነገሩን ነው፡፡ ብዙ ቢቀራቸውም ጅምሩ መበረታታት አለበት፡፡ ቢያንስ ድሮ ከምናውቀው ኦነግ፣ የተሻለ  ያካሄድ ምልክቶች ፣ እየሰማን እያየን ነው ፡፡

ከላይ በጠቀስኩ አምስተርዳም ዉስጥ ተካሂዶ በነበረው ስብሰባ ፣ ከተሰብሳቢው ዉስጥ አንድ የኦነግ ደጋፊ፤ ''በኢትዮጵያ ዉስጥ የሕዝብ ሰብአዊ መብትና እኩልነት ከተረጋገጠና ፣ ዲሞክራሲን ካሰፈን.....ወዘተ ኦሮሞ ለምን ከኢትዮጵያ ይገነጠላል ፣ ኦሮሞ ግንድ ነው ፣ ኦሮሞን ካለኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያን ካለ ኦሮሞ ማሰብ እንኳዋን አይቻልም፡፡ እንኳዋን ኦሮሞ ሊገነጠል ቀርቶ፣ ወያኔ ከአማራው መሬት እየቆረሰ ለባእዳንና ለማይገባቸው ክፍሎች ወስዶ ያከፋፈለውን መሬት ፣ ከሌሎች ወገኖቻችን ጋር ሆነን ታግለን እናስመልሳለን......ወዘተ'' ነበር ከሞላ ጎደል ያሉት ፡፡ እንደዚህ አይነት አስተሳሰብ ያላቸው በግለሰብም ይሁን በቡድን እየቀረቡን ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ክስተትን ፣ ''በሰላማዊ ጥርጣሬ'' ማመንም ሆነ መቀበል የሚቸገሩ እንዳሉ ባንክድም ፣ አክራሪዎቹ እንደዚህ አይነት በጎ ነገር መስማት እቅዳቸውን ስለሚያበላሽ አይቀበሉትም፡፡

የተለየን መስመር ከሚያራምድ ጋር ፣ መደማመጥ ፣ መወያየት መጀመር ፣ በጠላትነት መተያየት ማቆምና፣ ስለወደፊቱ በብሩህ ተስፋ ላይ የተመሰረተ ሕዝብን ያሳተፈ ግልጽ ውይይት መጀመር፣  የመጀርያው ብሩህ ተስፋ ነው፡፡

በዚህ አዲስ አካሄድ ኦነግ አሁን የጀመረውን መንገድ የውሸቱን  እንደ ''የዘዴ ለውጥ'' (a change of tactic)አድርገው የሚፈሩ ካሉም አንፈርድባቸውም ፡፡ ምክንያቱም ''ሰላማዊ ጥርጣሬ'' ያልኩት ፣ባለፈው ''በሕዝበ ውሳኔና'' በዴሞክራሲ ስም ወያኔ ሕዝብን አታሎ ኤርትራን ያስገነጠለበት ተመሳሳይ መንገድ መጥፎ ተመክሮ ስላሳለፍን ሁላችንም ዉስጥ ያ ጥርጣሬ ሊኖር ይችላል ፡፡   ካለፈው ተምሮ ተመሳሳይ ሁኔታ እንደገና እንዳይፈጠር መጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑ ብናምንም ፣ ህልም ተፈርቶ

ሳይተኛ አይታደርም እንደሚባለው ፣ ያለፈውን ስህተት እንዳንደግም በመፍራት ብቻ ወደፊት ሊገነቡ የሚገባቸውን በጎ ነገሮች በሙሉ ልንሸሽ አይገባም፡፡

አንዳንድ የተቃዋሚ ድርጅቶችና በውይይቱም ላይ የህብረቱ ተወካይ እንደነገሩን ፣ አነግን ወደ መሃል ለማምጣት ለብዙ ዓመታት የደከሙ ፣ በአሁኑ ሰአት ጀምረውት የነበረውን ሥራ፣ አጋዥ ሲያገኙና ትንሽ መስመር መያዝ ሲጀምር ደስ ሊላቸው ሲገባ፣ በዚህ ውይይት ቅር ከመሰኘት አልፈው፣ በዚህ ስብስብ ላይ `` ሕዝበ ማእቀብ`` እንዲጣል ጥሪ አስተላልፈው ነበር፡፡ ለዚህም የሰጡት ምክንያት ፣ ከላይ እንደተጠየቀው ፣`` <u>አነግ እስከ ዛሬ ያወጣውን የመገንጠል ፕሮግራም የልቀየረ ፤ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም የሚል ፡ ከሻቢያ ጋር ያበረና ፣ በሽግግር ላይ በነበረበት ወቅት ብዙ ወንጀል የሰራ</u> ....ወዘተ``የመሳሰሉት ጫን አድርገው ያቀርባሉ፡፡

ብዙዎቻችንን ግን ግራ ያጋባን ፣ ይህንን ምክንያት የሚያቀርቡት ወገኖች ፣ እራሳቸው ለብዙ ዓመታት ይህንን ከላይ የሚነግሩንን ምክንያቶች በሙሉ እያወቁ ፣ አነግን የመገንጠሉን ጥያቄ እንዲሰብና በህብረት ውስጥ ታቅፎ አብሮ እንዲሰለፍ ሲሞክሩ፣ ትክክል የሚሆንበትና ፣ ሌሎች ወገኖች ይህንኑ ተመሳሳይ ተግባር ሲሞክሩ ስህተት ለምን ይሆናል? መቃወም መብት ቢሆንም ፣ የአቅዋም ለውጥ ሲደረግ በቂ ማብራርያ ይጠበቃል ደግሞስ እውነት የሚሳካ ከሆነ ፣ ለሰላም ፣ ለፍቅር ፣ ለአብሮነታችን ብለው ለምነው ወደ አንድነት ማምጣት ከተቻለ ችግሩ ምንድነው? ወይስ ቀፎ ዉስጥ የነበሩት ተራብተው እነሱንም አቅፈዋቸው ይሆን ?

ትላንት ተጨቁነሃል፤ ተገፍተሃል፤ በእኩልነት አትታይም ፣ ተነስ ...መብትህን እስከመገንጠል እናውቅልሃለን ተብሉ ከሚያስፈልገው በላይ እንዳልተቃኘ፤ አሁን ደግሞ የተቃራኒውን ሌላ ጠርዝ ተይዞ ፣ እራሳቸውን ከአክራሪዎች አንድ እርምጃ አርቀው ፣ ከሌላው ሕዝባችን ጋር ፣ በሰላማዊ መንገድ ችግርን ለመፍታት እየሞከሩ ያሉትን ፣ መቃወምና ይህንን ውይይት የሚደግፉን ጭምር በሃገር ከሃዲነትና በተገንጣይነት መድቦ መንቀሳቀስ መጀመር ማንም የማመዛዘን እዕምሮ ያለው መቀበል ያዳግተዋል ፡፡ የመጀመርያው መሳሙም ሳያስፈልግ ፣ ያሁኑ መንከሱ ቀርቶ ፣ እጅ ለእጅ ተጨባብጠን ተደጋግፈን ትግሉን ብንገፋ ልሁላችንም ይበጀናል፡፡

<u>ግንቦት7 ነገ ከአነግ ጋር</u> <u>ስምምነት ላይ ደርሶ</u> ፣ ሃገራችንና አንድነታችንን አደጋ ላይ የሚጥል ውል ቢዋዋል ፣ ሃገር የሚያፈርስ የሚያስገነጥል ድርድር ቢጀምር ፣ ከሕዝብ የተደበቀ ስምምነት ቢያደርጉ ፣ተቃውሞዋችንን በግልጽ ማሰማት አግባብ ነው፡፡ አነግ በፕሮግራሙ ላይ ያሰፈረውን የመገንጠል የመሳሰሉትን የሚለያዩን፣ አንድነታችንን የሚጎዱ ፣ ለትግላችን እንቅፋት ከላይ የተጠቀሱትን እዲቀይር ግፊት ማድረግ አግባብም አስፈላጊም ነው፡፡ ሳያውቅ ተሳስቶ የነበረውን አውቆ ከሚያጠፋው፣ የአንድነት ጥቅም የገባውን ከአክራሪው ፣ ጭፍራውን ከአለቃው እያየን ችግሩን መቅረብ ሲገባን ፣ እራሱን

በልዩነት ዙርያ መወያየትን መቃወም፣ ችግሩን ከማባባሱም በላይ ፣ ጨቅላ በሆነው የዲሞክራሲ ባህላችን ውስጥ አረም መዝራት ነው ፡፡

ለሃገራችን ህልውና ዋስትና ለመስጠት ፣ መወያየትን መቃወም ሳይሆን፣ በሚረባውም በማይረባውም ተከፋፍሎና ተበታትኖ፣ ተዳክሞ ያለውን የአንድነት ሃይሉን ማሰባሰብና ማደራጀት ወደፊት በሚፈጠረው ሰፊ መድረክ ላይ የራሱን ሚዛን እንዲደፋ የራስን የቤት ሥራ መስራት ነው፡፡

በሌላ መንገድ ግንቦት7ም ሆነ አብረዋቸው ውይይት የጀመሩት ምንም የሚፈሩትና የተደበቀ ዓላማ እስከሌላቸው ፣ የውይይት መድረኩን ማስፋትና ሌሎች ተደራጅተው ያሉና ፣ ወደፊት የሚመጡትን ለማካተት ማመቻቸትና በሩን በደንብ መክፈት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ የሚጠቅመው ፣ በተደጋጋሚ በቅንነትም ጭምር ጉዳዩ ከሚያሳስባቸው ወገኖች ከሚቀርቡት ሃሳብ ፣ ወያኔ ስልጣን ላይ ሲወጣ የተጠቀመበትን ስልት እንደገና እንዳይደገም ዋስትና መስጠት ብቻ ሳይሆን ስጋታችንንም ይቀንሳል፡፡

እዚህ ላይ ከብዙ ወገኖች በቅንነት የሚቀርቡ የሚደመጡ ስጋቶች ሳልጠቅስ አላልፍም፡፡ ``ኦሮሞ ብዙ የሕዝብ ብዛት ስላለው በድምጽ ብልጫ አሸንፎ ሊገነጠል ይችላል``፡፡ ``ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ከተካሄደ አነግ ያሸንፍና ኦሮሞ ያልሆኑ ሕዝባችንን ይበቀላል`` ...ወዘተ አይነት ፍራቻ አልፎ አልፎ ይደመጣል፡፡ አገዛዙም ሆነ አክራሪዎች ይህንን ፍርሃት በውስጣችን እንዲሰፍን የማይቆፍሩት ድንጋይ የለም፡፡ በሌላ ጎኑ እንደዚህ አይነት ቅዠት ያላቸው በየትኛውም ህብተረተ ሰብ ውስጥ የሉም ማለትም አይደለም ፡፡

በመጀመርያ የኦሮሞን ሕዝብ በሙሉ በአነግ መነጽር እንድናይና እንድንጠረጥር የሚገፉንን ከላይ የጠቀስኩዋቸውን አክራሪዎችና ፣ አገዛዙን ለጊዜው ትተን፣

የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ያለውን ትስስር የሚያከብር በኢትዮጵያነቱ የሚኮራ ሕዝብ ነው፡፡ ያለፈ ታሪኩም ቢሆን ዛሬ አዳዲስ ወጣት መሳፍንቶቻችን ሊነግሩን እንደሚፈልጉት ሳይሆን ፣ የኦሮሞ ሕዝብ በነበረው የሃገር ግንባታ የራሱን አስተዋጾ እንደሌላው ሕዝባችን አድርጎዋል፤ ሃገር አስተዳድረዋል፣ በብዙ ሃላፊነት ቦታ ተሳትፈዋል፣ በተደጋጋሚ የሚነሱት ራስ ጎበና ብቻ ሳይሆኑ ፣ ከእሳቸው ጋር በሺዎች የሚቆጠሩ ፈረሰኞችን አሰልፈው ከአፄ ሚኒሊክ ጎን ተሰልፈው ነበር ፡፡ በንጉሥ ሃይለ ሥላሤ ዘመን ታማኝ የክብር ዘበኛ ሆነው የዘውዱን ስርዓት ከተቀናቃኞቻቸው ይጠብቁላዋቸው የነበሩት አብዛኛዎቹ ኦሮሞዎች ነበሩ ፣ ከውጭ ወራሪዎች የሃገርን ዳር ድንበር ላለማስደፈር ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወገኖቻቸው ጎን ተሰልፈው እልፍ አእላፍ መስዋእትነት ከፍለዋል ፡፡ ይህም እስከ ትላንቱ የባድመ ጦርነት ታይቷል ፣ ወደፊትም ይቀጥላል፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው ወገኑ ጋር ተዋልዶዋል፣ ተቀላቅሏል፡፡ ማነው የኦሮሞ ደም የሌለበት? ፡፡ ስለዚህ ካለማወቅ ኦሮሞ በሙሉ አነግን ይደግፋል፣ ወይም ሊገነጠል ይችላል የሚለው ከጥቂቶች አካባቢ ያለው ፍራቻ ሊኖር

አይገባም ፡፡ በሌላ መንገድ ጭቆናና በደል እስካለ ለመታገል ውክልናና የቁጥር መብዛት አያስፈልግም ጥቂትም ቢሆኑ በአግባቡ ቅሪታቸውን ለማህበረሰባቸው ማሰማት መብታቸውን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ እራሳቸውን ኢትዮጵያዊነትን ሰጪና ነሺ አድርገው የሚያቀርቡ፣ አንዱ ታማኝና ሌላው ተጠርጣሪ ፣ አንዱ ጎበዝ ተዋጊ ሌላውን ፈሪ ፣ አንዱን ክፍል ገዢ ሌላው ተገዢ አድርገው ለመቅረብ የሚፈልጉት፣ ሕዝባችንን በእኩልነት ለማየት ችግር ያለባቸው ዘረኞችን ከሚረጩት መርዝ እንጠንቀቅ ፡፡ የነዚህ ክፍሎች አደጋ ፣ በግልባጩ መሆኑ እንጂ፣ ከመገንጠል በስተቀር ሌላ አማራጭ የለም ብለው ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጎን ተሰልፈው ለያፈርሱን ከሚጥሩት አክራሪዎች ጋር የቅርጽ እንጂ የይዘት ልዩነት የላቸውም፡፡

እነዚህ ሁሉ የጎሳ ድርጅቶች ፣ስርአቱ የፈለፈላቸውም ሆነ እራሳቸው የተደራጁት ('' ነጻ አውጪዎቹን'' ጨምሮ)፣ ባይፈጠሩ ባይኖሩ፣ወይም በህብረ ሕዝብ ድርጅቶች ውስጥ ተደራጅተው ጎደለን የሚሉትን መብታቸውን ቢጠይቁ ጥሩ ነበር፡፡ ነበር ምኞት ነው አልሆነም ፡፡ ፈለግንም አልፈለግንም አሁን ከኛ ቁጥጥር ውጭ ናቸው፡፡ እነዚህ ክፍሎች በቡድን የደረሰብን ችግር አለ ሳንገነጠል፣ አንቀጽ 39 ሳያስፈልገን፣ ከሕዝባችን ጋር ይህንን ሁኔታ መክረን ዘክረን ለወደፊቱ ለሁላችንም አስተማማኝ ስምምነት ላይ በጋራ እንድረስ ብለው ፈቃደኝነታቸውን ቢያሳዩ ፣ እኛ በምንፈልገው አደረጃጀትና፣ መንገድ ስላልሄዱ በጸረ ኢትዮጵያዊነት ወይም በተገንጣይነት ልናያቸው አይገባም ፡፡ በሁሉም ሕዝባችን ዉስጥ እምነት ይኑረን፡፡ ውይይቱ መለያየትን ፣ መገንጠልን ለማስቀረት ከሆነና ይህንን በራሴ ኪሳራ እሞክራለሁኝ ብሎ ሌላው ከተነሳ ፍርሃቱ ምንድነው? ካልተቻለ ይቀራል፡፡ መሰረታዊው እውነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ኦሮሞን ጨምሮ በ97ቱ ምርጫ አንድነቱን እንደሚፈልግ ግልጽ አድርጎዋል ፡፡

ያ የመገነጣጠል ፍርሃት እውነት ሊሆን የሚችለው ፣
--የአንድነት ክፍሉ ልዩነቱን አቻችሎ መሰባሰብና መደራጀት ካልቻለ፡፡
--አሁን እንደምናየው ከአክራሪዎች እራሳቸውን አግልለው ወደ አንድነቱ ለመቅረብ የሚሞክሩትን ቀንድ ቀንዳቸውን መተን ገፍተን መልሰን ከአክራሪዎች ጋር አብረው እንዲሰለፉና እንዲጠናከሩ ስናደርግ ፡፡
-ነገሮችን ከጊዜያዊ ድርጅታዊ ጥቅምና ፣ ከፓርቲ ፖለቲካ ባሻገር ፣ በብሄራዊ አጀንዳ ዙርያ መሰባሰብና ፤ በረጅሙ ዘለቄታዊ የጋራ ጥቅማችን ላይ በጋራ ማተኮር ሲሳነን ፡፡
--በአገዛዙ ለሚሰቃዩት ፣ ለሚታሰሩት ፣ በረሃብ በስደት ለሚሰቃዩት፣ ለሁሉም ወገኖቻችን እኩል መቆርቆር ሲሳነን፡፡ ----
''እኛና እነሱ'' ብለው ለሚከፋፍሉን ዘረኞች ጀሮ መስጠት ስንጀምርና በነሱ መንገድ ከቀጠልን ፣ ያ የፈራነው አደጋ ሊመጣ እንደሚችል በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ የተጀመረው ውይይት ሊደገፍና ሊበረታታ ይገባል፡፡ ለዓመታት በተዳዝንባቸው ተመሳሳይ መንገድ ፣ ቃላት በመወራወርና ፀጉር በመሰንጠቅ ይበልጥ በታተነን አራራቀን እንጂ ችግሩን አላቃለለልንም፡፡ያውም እንደዚህ አይነት ግልጽ ውይይት ሲገኝ ፣ ስብሰባውን

አኩርፎ መቅረት ወይም ሰዎች እንዳይሄዱ ማሳደም የድክመት ወይም ደጋፊዎቻቸው እውነቱን ተረድተው አቅዋም እንዳየውስዱ ፍራቻ ካልሆነ? በማንኛውም ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ፣ አዳምጦ ፣ ጠይቆ ካልተስማማው መቃወምና ፣ አማራጩንም ማሰማት ነው መለመድ ያለበት፡፡
እንዴ የተሳሳተና ፣ ያኮረፈ ፣ ወደትግሉ መመለስ አይችልም ልንል አይገባንም ፡፡ ሁላችንም በአንድ የታሪክ አጋጣሚ የየራሳችን ስህተቶች ሰርተናል፡፡ ዛሬ እነሱን የምንከሳቸውን ስህተቶች በከፊል የኛም ስህተቶች ነበሩ፡፡ በግል ወይም በቡድን በደል ደርሶብናል ብሎ ቅሬታን ማሰማት ፣ መወያየትና ለተሻለ ስርአት አብሮ ለመገንባት ማበር፣ መበረታታት መደገፍ ያለበት ጉዳይ ነው ፡፡ ትላንት በቡድን በደል ደርሶብናል ፣ ድምጻችንን የሚያሰማልን ስላጣን ተገደን በአንድ አካባቢ ተደራጅተናል ብለው ተደራጅተው ጥቃትን የተከላከሉት ኢትዮጵያን ካዳቹ ብሎ የተቃወመ የለም ፡፡እንዲያውም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ነው ጥቃቱን አብሮ የታገለው፡፡ ተመሳሳይ ነገር መቼም ፣የትም ሊከሰት ይችላል፡፡

አገዛዙን በጋራ አስወግዶ በቦታው ፣ ፍትህ፣ እኩልነትና ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን ለመገንባት ፣ ያለፉበትን መንገድ ትተው ከሌሎች ወገኖቻቸው ጋር ሊሰለፉ የመጡትም ሆነ ወደፊት የሚመጡትን ፣ ብርታቱንና ቁርጠኝነቱን እየተመኘንላቸው ፣ አሁን እየቀረቡ ያሉትም፣ ይህንን የወገኖቻችንን ልብ ቅር ያሰኘ ፣ ለአገዛዙና ፣ ሕብረታችንን በበጎ ለማያዩት ለባዕዳን በር የሚከፍት በፕሮግራማችሁ ላይ የሰፈሩትን ፣ ``መገንጠልን`` እስከወዲያኛው ከገጹ ገንጥላችሁ ከፕሮግራማችሁ በቀይ ቀለም ሰርዛችሁ ሕብረታችንን ተቀላቀሉ ፡፡ ይህንን ለማድረግ ሌሎች እንቅፋት ከሆኑባችሁ ? የራሳችሁን ግልጽ መግለጫ በማውጣት፣ እየተጠየቀ ያለውን የወገኖቻችሁን መልስ መልሱ፣ ጠላትንም የሚገባበትን ቀዳዳ ድፈኑ ፡፡

በተረፈ የግንቦት7ም አመራሮች በተደጋጋሚ እንደቀረበው ወቀሳ ስለስብሰባው የራሳቸውን አቅዋምና ከሌላው ክፍል የሚጠብቁትን መልካም ተስፋ ይንገሩን እንጂ ፣ ስለኦነግም ሆነ ስለ ኦብነግ ሆነው ማብራርያም ሆነ ማስተባበያ መስጠታቸው በቅንነት ከታየ ለበጎ መሆኑ ቢታመንም በአሰራር ሁለት የተለያዩ ድርጅቶች ማንጸባረቅም ሆነ መግለጫ ማውጣት ያለባቸው የየግላቸውን ነው፡፡ህብረት ወይም ጥምረት፣ ወይም ተስማምተው ቃለ-ጉባኤ የተፈራረሙበትን በጋራ መግለጫ እስካልሆነ ማለቴ ነው፡፡ ሌላው በኢትዮጵያ አንድነት ስም ባለፈው ታሪካችን ውስጥ ብዙ የምንኮራበትም ሆነ አሉታዊ ገጽታዎች ቢኖሩትም ፣ በነዚህ አሉታዊ ገጽታዎች ምክንያት ፣ በአንድነት የገነባናቸውንና የምንኮራባቸውን በጎ ነገር ሁሉ ሊያደበዝዝብን አይገባም፡፡ በዚህም ምክንያት አንድነት ሲነሳ ሊከፉ የሚችሉ ወገኖች ሊኖሩ ይችላል ተብሎ ይህንን ቃል መሸሽ አያስፈልግም ፡፡ የሸሹትን እራሳቸውን ወደ አንድነቱ ለማምጣት እየደከማችሁ ሌሎች ቃሉን ለተሳሳተ ተግባር ተጠቅመውበት ስለነበር ብቻ ቃሉን ላለመጠቀም መሸሽ በአንድነት ስም የተሰሩትን በጎ ነገሮች በሙሉ ማደብዘዝ እንዳይሆን፣ ቃሉም መፈክራችንና ግባችን ስልሆነ መጠቀም አለብን፡፡

ለማጠቃለል ከላይ እንደገለጽኩት ፣ እኛም በሰከነ አዕምሮ ፣ ወደፊት እንዳናይ ባለፈው ላይ ብቻ አተኩረን ፣ ዋናውን የሕዝባችንን ችግር እረስተን ፣ አዳዲስና የቆየ ቁርሾና ቂም በቀል እየኮተኮቱ ሕዝባችንን ለማራራቅ ጥላቻ የሚያራግቡትን ከሁለቱም ጎራ ያሉትን አክራሪዎች ጆሮ ሳንሰጥ፣ ለሃገራችን ለሕዝባችን የሚጠቅም ይህ የተጀመረውንም ሆነ ሌሎች የአንድነት ሃይሎች እያደረጉ ያሉትን ጥረት ፣ በማንኛውም መንገድና፣ በየትኛውም ቡድን ያሉትን፣ ኢትዮጵያዊነትና ፣ አብሮነትን፣ የሚያጠናክር እስከሆነ ድረስ ሁሉንም ፣ መደገፍ ፣ መምከርና ማቀራረብ ይኖርብናል እንጂ እንደ መሳፍንት ዘመን ጎራ ለይተን ከፊሉ ሕዝባችንን በጥርጣሬና በጥላቻ እያዩ ለሚከፋፍሉን ጆሮዋችንን አንስጥ ፡፡ ለተጀመረው የሕዝብ ጥያቄ ሳንከፋፈል አብረን ከሕዝባችን ጎን እንሰለፍ ፡፡

ኢትዮጵያ በልጆቿ አንድነት ታብባለች

አብሮነታችን ይዘልቃል፡፡

ብስራት ኢብሳ

ለማንኛውም አስተያየት፣ tebaber@gmail.com